# የአጸደ ህጻናት ትምህርት የሚጀምረው ከ ጃምፐ ስታርት ነው::

## ከነሃሴ 19 -23, 2019 በየቀኑ ከጥዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ ቀኑ

ጃምፐ ስታርት ለአንድ ሳምንት ጊዜ የአጸደ ህጻናት ተማሪዎች ልምድ እንዲያገኙ በነጻ የሚሰጥ ፕሮግራም ነው:: ህጻናት አዲሱን ት/ቤታቸውን: ህንጻውንና ሰራተኞችን እንዲያውቁና በመደበኛው የት/ጊዜ የሚያደርጉትን ተግባራት የሚለማመዱበት ነው::

ጃምፐ ስታርት የአጸደ ህጻናትን ተማሪዎች እንደሚከተለው ይረዳል:

- አስደሳች የትምህርት ልምምድ
- በየእለቱ በት/ቤት ውስጥ የሚደረጉትን ተግባራት ይለማመዳሉ: ይማራሉ::
- በመማሪያ ክፍልና በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ምቾት እንዲሰማቸው ያደርጋል::

ጃምፐ ስታርት ወላጆችን እንደሚከተለው ይረዳል::

- እድሜያቸው ከልጆቻቸው ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ልጆች ካሏቸው ወላጆች ጋር ይተዋወቃሉ::
- ርዕሰ መምህሩንና ሰራተኞችን በመገናኘት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ::

ጃምፐ ስታርት ሰራተኞችን እንደሚከተለው ይረዳል::

- ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ማጠናከር ይጀምራሉ
- የተማሪዎችን ልምድና ጥንካሬ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል::

# የጃምፐ ስታርት መሰረታዊ ዕውነታዎች

አብዛኛዎቹ የሲያትል የአንደኛ ደረጃና ከ K-8 ያሉ ት/ቤቶች የጃምፐ ስታርት ፕሮግራም ይሰጣሉ:ጃምፐ ስታርትን ለመከታተል ተማሪዎች በተሳታፊ ት/ቤቶች ሊመደቡ ይገባል::

- ት/ቤቶች ለ እንግሊዘኛ የ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ድጋፍና ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጣሉ::
- ወላጆች ልጆቻቸውን በየቀኑ እንዲያመጡና እንዲመልሱ ይጠየቃሉ:: የትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም::
- ት/ቤትዎ ምግብንና ሌሎች ልጅዎት የሚፈልጋቸውን ጉዳዮችን በተመለከተ ያነጋግርዎታል::

# የጃምፐ ስታርት ምዝገባ

እያንዳንዱ ት/ቤት የየራሱን የመመዝገቢያ ቅጽ በመላክ የሚሰበስብ ሲሆን የህንኑ የጃምፐ ስታርት መመዝገቢያ ቅጽ በኮምፒዉተር ኦንላይንም መሙላት ይቻላል:: እባክዎትን ቅጾቹን በቀጥታ ለት/ቤትዎ ከሰኔ ወር መጨረሻ ቀደም ብለው ይመልሱ:: አብዛኛዎቹ ት/ቤቶች ሃምሌ እና ነሃሴ መጀመሪያዎቹ ላይ ዝግ ናቸው:: ሰራተኞች ነሃሴ 14 ወደ ስራ ይመለሳሉ::

ለበለጠ መረጃ እባክዎትን ሜሪ ፊከስን በሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የቅድመ መደበኛ ት/ክፍል ቀጥሎ ባለው አድራሻ ያግኙ:

☎ (206) 252-0127

💻 mpfickes@seattleschools.org